

# ጳውሎስ በኢየሩሳሌም

- ጳውሎስ ወደ ኢየሩሳሌም ተጓዘ። በዚያም አንዳንድ አይሁዳውያን ከሕጋቸው ጋር የሚቃረን ትምህርት እንደሚያስተምርና ወደ ምኩራቦቻቸውም እንዲገቡ ያልተፈቀደላቸውን አሕዛብን እንሚያስገባ ጠቅሰው ክስ መሰረቱበት። ከተማይቱ በሙሉ በዚህ ምክንያት በተነሳው አመፅ ታወከች። ብዙ ሰዎችም የሆነውን ነገር ለማየት ከያሉበት በሩጫ ተሰበሰቡ። ጳውሎስን ለመግደልም ሙከራ አደረጉ። ሆኖም በሮማውያን ወታደሮች ሕይወቱ ተረፈችለት። የተሰበሰበው ሕዝብ እጅግ ሞገደኛ ስለነበር የሮማውያን ወታደሮች ተሸከመው ወሰዱት።

- ጳውሎስ የቤተ መንግስቱን ደረጃ እየወጣ ሳለም ለሕዝቡ አንዴ ንግግር እንዲያደርግ ፍቃድ ጠየቀ። በወታደሮች ተከቦም ራሱን የሚከላከልበትን ንግግር ማድረግ ጀመረ። በመጀመሪያ ስለመለወጡ አወራ። ኢየሱስ ክርስቶስ ለአሕዛብ ወንጌልን እንዲሰብክ እንደመረጠው እስኪናገር ድረስ በፀጥታ ያደምጡት ነበር። ሆኖም ልክ ስለዚህ ጉዳይ መናገር ሲጀምር እንደገና ከፍተኛ ሁካታ ተነሳ። እጅግ በጣም በአስከፊ ሁኔታም ሕዝቡ መጮህ ጀመር። አዛዡም ጳውሎስን ወደውስጥ አስገብተው እንዲገርፉት አዘዛቸው።

- ጳውሎስ የሮም ዜግነት እንዳለው አያውቁም ነበር። በዚያን ጊዜ ደግሞ የሮም ዜግነት ያለውን ሰው መደብደብም ሆነ መግረፍ በሕግ አይፈቀድም ነበር። ጳውሎስ ስለ ዜግነቱ ሲናገር ፈሩ። በእርሱ ምን እንደሚያደርጉም ማሰብ ጀመሩ። ሮማዊው አዛዡም ወደአይሁዳውያን ሸንጎ ተወስዶ ጉዳዩ በዚያ እንዲታይ አዘዘ። ጳውሎስም ፈሪሳዊ እንደሆነና በሙታን ትንሳኤ እንደሚያምን ሲናገር በሸንጎው ውስጥ በነበሩ ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን መካከል ከፍተኛ መለያየት ተፈጠረ። በዚህ ምክንያትም እንደገና ከፍተኛ ሁከት ተነሳ። ሮማዊው አዛዡም ጳውሎስን ወደ ወታደሮች ካምፕ ይዘውት እንዲሄዱ ትዕዛዝ ሰጠ።

- በዚያች ሌሊት ጌታ ኢየሱስ በጳውሎስ አጠገብ ቆሞ አበረታው። ማለትም አይዞህ አለው። ወደሮም እንደሚጓዝና በዚያ ላሉ ሰዎች ስለኢየሱስ እንደሚነግራቸው ነገረው።

- ❋ በዚህ መካከልም ጳውሎስን ለመግደል አይሁዳውያን ያሴሩ ነበር። ሆኖም የጳውሎስ የወንድሙ ልጅ ስለዚህ ሴራ ሲሰማ ለባለስልጥናት መረጃ ሰጣቸው። ሮማዊው አዛዥም ጳውሎስን ወደ አገረ ገዢው ፊሊክስ ለመላክ ወሰነ። ምንም ጉዳት እንደማይደርስበት እርግጠኛ ለመሆንም በ200 ወታደሮች፣ በ70 ፈረሰኞችና ጦር ባነገቡ በ200 ሰዎች ታጅቦ እንዲጓዝ አደረገ። ጳውሎስ ፈረስ እየጋለበም ከምሽቱ 3:00 ሰዓት ጉዞ ጀመሩ።

*ይህን የመፅሐፍ ቅዱስ ታሪክ በሐዋርያት ስራ ከምዕራፍ 21:17 እስከ ምዕራፍ 23:24 ባለው ክፍል ውስጥ ማንበብ ይቻላል።*

http://gardenofpraise.com